


መለያ ቁጥር (ID) **0591**

በአቶ መለስ ሰለሞን መሓሪ (B.Sc, M.Sc)

Tel:- +251914708685

+251914617441

Email: - meles.solomon@moh.gov.et

ሰነ 2012 ዓ.ም

## ምሥጋና

በታሪክ ለመጀመርያ ግዜ በመንግስት ደረጃ ሀገር በቀል ባህላዊ ዕርቅ ስርዓቶች ትኩረት በመስጠት ወደኋላ በመመለስ በአዲስ እንዲነሱ እና እንዲታዩ ላደረገው የሰላም ሚኒስቴርና እና ዕርቅ ኮሚሽን ላዘጋጁት ለትውልድ የሚተላለፍ ታሪካዊ መልካም ስራ እና በዕርቅ ስራዎች ለሚሰማሩ ዜጎች እና የዕርቁ ባለቤት ማሕበረሰብ ለተሰጠው ዕድል ከፍተኛ ምስገና ለማቅረብ ይገባል፡፡

ሁለተኛ በግል ለብዙ ግዜ የሰራሁትን ባህላዊ የእንደርታ ዕርቅ ስነ ስርዓት ለኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን ለዓለም ለማሳወቅ እንዲቀርብ ለተሰጠኝ የመወዳደርና የመሳተፍ ዕድል በጣም ከፍተኛ ምስገና ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

## ማውጫ ገፅ


ምዕራፍ - አንድ ........ 1
“ዕርቂ እንደርታ” ........ 6
የእንደርታ ዕርቅ የት አከባቢ የሚገኝ የዕርቅ ስርዓት ነው? ........ 6
ምዕራፍ - ሁለት ........ 8
ዕርቂ እንደርታ ባህላዊ ስነ-ስርዓቱ ምን ይመስላል? ........ 8
2.1 የእንደርታ ዕርቅ ኣጀማመር ........ 8
2.2 የእንደርታ ዕርቅ ይዘትና ሂደቱ ........ 9
2.2.1 የእንደርታ ዕርቅ ወሰን ተሻጋሪ መሆኑ ........ 9
2.2.2 “ኣቦ ገሪብ” (ቋሚ የወሰን የሀገር ሽማግሌዎች) ........ 9
2.2.3 በሽምግልና የሚሳተፉ ፆታ፣ ዕድሜ፣ እምነትና ስልጣን ........ 10
2.2.4 የእንደርታ ዕርቅለቅድመ ግጭት መፍትሄ የሚሰጥ መሆኑ ........ 10
2.2.5 የእንደርታ ዕርቅ እስካሁን አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ ........ 10
2.2.6 የእንደርታ ዕርቅ የዘላቂ ሰላም ተመራጭ ሥርዓት መሆኑ ........ 10
2.2.7 የእንደርታ ዕርቅእንደ የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ ያገለግል ነበር (እንደ ሰበር) ........ 10
2.2.8 የእንደርታ ዕርቅ ሰፊ ተጠቃሚነት፣ ተቀባይነትና ታዋቂነት አለው ........ 11
2.2.9 የእንደርታ ዕርቅ ለሁሉም በእኩልነት ሳይሸፋፍን የሚዳኝበት መሆኑ ........ 11
2.2.10 የእንደርታ ዕርቅ ለሁለት በመባል ይታወቃል ........ 11
2.2.11 የእንደርታ ዕርቅ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች ያስወግዳል ........ 11
2.2.12 የእንደርታ ዕርቅ ለሁሉም የማህበረሰብ መደብ ያገለግላል ........ 12
2.2.13 የእምነት (ሃይማኖት) ልዩነት እና እኩልነት ያከብራል፣ ያስማማል ........ 12
2.2.14 የእንደርታ ዕርቅ ከዘመናዊ ሕግ ያለው ትስስር (ዝምድና) ........ 12
2.2.15 የዕርቅ ጥቅሞች ........ 12
2.2.16 የእንደርታ ዕርቅ ከግጭት ኣፈታት ውጪ ሰፊ አገልግሎት አለው ........ 13
የእንደርታ ዕርቂ ........ 13
ምዕራፍ - ሶስት ........ 13
የእንደርታ ዕርቅ አሁን ያለበት ሁኔታ ........ 13
ምዕራፍ - አራት ........ 14
ስለ ዕርቅ እንደ ሀገር ምን ይደረግ ........ 14
ምዕራፍ - አምስት ........ 15
መደምደምያ ........ 15
ዋቢ ........ 15

## መግብያ

የሰው ልጅ ከዓለም ፍጥረታት ሁሉ የተሻለ አስተሳሰብና ባለ ብሩህ አእምሮ፣ አስተዋይና ተማሪ በመሆኑ የሚያጋጥሙት ችግሮች፣ ፈተናዎች፣ አካባቢው ወደ ራሱ ጥቅም ለመለወጥ ብዙ ፈጠራዎች እና ብልሃቶች ሊፈጥር ችለዋል፡፡

የሰው ልጅ አሁን ከደረሰበት የአስተሳሰብ ደረጃ ከመድረሱ በፊት፣ በስርዓት አልበኝነት ዘመን፣ ሕግና ስርዓት ባልነበረበት፣ የሰው ልጅ ክብርና ሰብኣዊ አስተሳሰብ ያልነበረበት ዘመናት አልፈዋል፡፡ በዚህ በጥንት ዘመን ከመተባበር፣ መተጋገዝ፣ ፍቅርና ሰላም ይልቅ ግጭት፣ ሁሉም ለኔ እና በኔ፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ፣ እኔ የተለየሁ ፍጡር ነኝ፣ ብቻየን ልብላና ልኑር፣ አኔ ነኝ ጀግና፣ እኔ ነኝ ገዢ በሚሉ የፉክክር፣ አለመግባባትና እና የእርስ በርስ ግጭቶች በመፍጠር በሰዎች ላይ በጉልበት ይሁን ተፅእኖ በመፍጠር ብዙ የኪሳራ ዘመን ታሪኮች ተስተናግደዋል፡፡ ሰብ ከሰው ጋር በግል፣ በቡድን፣ በጎሳ፣ በአከባቢና ከብሁር አልፎ ሃገራት ከሃገራት ጎራ በመፍጠር በአለማችን በጣም አስከፊ፣ ሰፊና ለትውልድ የሚተላለፍ መጥፎ አሻራ ያስቀረ፣ የብዙ ዜጎች ሂወት የቀጠፈ የአንደኛና ሁለተኛ የዓለም አስከፊ ጦርነት ታሪክ አሳልፈናል፡፡

የዓለም ህዝቦች ያሳለፉት የእርሰ በርስ በርስ ግጭት ታሪክ በተመሳሳይ በአህጉራችን ይሁን በሀገራችን በተመሳሳይ በጎሳ፣ በብሄር እና በእምነት ግጭቶች፤ የኋላ ቀር አስተሳሰቦች እና ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች ሰው በመበደል፣ በመግደል፣ ደም መላሽ እየተባለ እንደ ጅግንነት፣ ጀብዱ እንደተሰራ የሚመሰገንበትና የሚሞገስበት ታሪክ አሳልፈናል፡፡

ከረጅም የኋላቀር አስተሳሰብና ድንቁርና በሂደት የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣቱ ምክንያት፣ የሃይማኖት ተፅእኖዎች፣ የመስተዳደራዊ ስርዓተ መንግስት መጀመር ጋር ተያይዞ፤ ሰው ሰው በመግደሉ ሊወቀስ፣ ሊወገዝ ሊቀጣ እና ከክፋት ምንም የሚገኝ ነገር እንደሌለ መረዳት ተጀመረ፡፡

በመተባበር፣ በመደጋገፍ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎችና ጥቃቶች በቀላሉ መከላከል እንደሚቻል በማየት እርሰ በርሱ መተሳሰብ አብሮ መኖር እና ብዙ ስርዓተ ክብሮች ሊተገብር ጀምሮዋል፡፡ በዚህም መሰረት የተሻለ አስተሳሰብ፣ መስተዳደር ሲጀምሩ በጉልበት፣ በዓመፅ እና በስርዓት አልበኝነት ሳይሆን የሚተዳደሩበት ሕግና ስርዓት እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡ በማህበረሰቡ ግፉትና ፍላጎት የሰው ልጅ 1ኛ በእምነት (በሃይማኖት) እንዲኖርና እንዲገዛ 2ኛ የስልጣን እርከን ስርዓተ መንግስት የመስተዳደር ሕግ እያደገ መጥተዋል፡፡ የስርዓተ መንግስት ባህላዊ የፍትህና ሕግ በመፍጠር ሊተዳደር ጀምረዋል፡፡ ከቅድመ ልደተ ክርስቶስ ጀምሮ ህዝብ በሕገ ኦሪት፤ ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በሕገ ሃዲስ ኪዳን በሕገ ልቦና እና በተፃፈ ሕግ ይተዳደር ጀመር፡፡ በሕገ ዞሪት ዓይን ያጠፋ ዓይኑ እንዲጠፋ፣ እጅ የቆረጠ እጁ እንዲቆረጥ ወዘተ የነበረው

በአዲስ ኪዳን ተሽሽሎ በግራ የመታህ መቀኙህ ስጠው፣ ክፉ ለሰራህ ጥሩ፣ እሳት ሁኖ ለመጣ ውሃ ሆነው ጠብቀው የሚለውን ሲተገበር መጥተዋል፡፡

በግዜ ሂደት እየታሻሻለ ከባህላዊ ሕገ ልቦና (ያልተፃ) ወደ ዘመናዊ ሕግ እየተሻገረ መጥቶ አሁን ወዳለንበት ዘመን ደርሰናል፡፡ አብዛኛው የዓለም ሳይንሳዊ ፈጠራዎችና ዘመናዊ ስርዓቶት መነሻቸው ከሃይማኖት እና ባህላዊ ስርዓቶች መሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ስለዚ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ለዘመናዊ የሕግ ስርዓት መነሻ ስለመሆናቸው እንደመሳያ በዘመናዊ ሕግ ልዩነቶች፣ ግጭቶች በዕርቅ ለማየት በወንጀል መቅጫ ሕግ፣ በፍትሃብሄር ሕግ፣ በቤተሰብ ሕግና ገላጋይ ዳኝነት በስርዓት በፅሁፍ ተፍሮ ይገኛል፡፡

ሰው ሰውን እየበደለ አይኖርምና ጉልበተኛ ይደክማል፣ ሃብታይ ይደሀያል፣ ባለ ብዙ ጎሳ ያንሳል፣ ባለ ግዜ ግዜ ይክደዋል በመጨረሻ ሰው ሰው ነውና ያልፋል፣ ታሪክይሆናል፡፡ ስለዚ ሰው ከማለፉ በፊት መጥሮ ታረክ፣ መጥፎ አሻራ ትቶ ቢሄድ ለትውልድ የሚተርፍ ክፉ ዕዳ ትቶ ላለመሄድ ይጠነቀቅ፣ ስርዓት ሊፈጥር፣ ደካሞች በሰላም የሚኖሩበት ስርዓት ሊፈትሩ ችለዋል፡፡

ኣበው እንደሚያስረዱት "ከረጅም የእርሰበርስ ግጭት በኂላ በሂደት የተሸለ አስተሳሰብና ዕድገት በመፈጠሩ ምክንያት ከጥላቻ፣ ከግድያ፣ ከቂም በቀል እና የክፋት ፉኩኩር ውድቀት ካልሆነ በስተቀር አንዳች ጥቅም እንደማይገኝበት በማስተዋል፤ የሰው ልጅ በማወቅ ይሁን ባለማወቅ ሲያጠፋ ጥፋቱ በመድገም ሳይሆን ጥፋቱ በማረምና በማስተማር በዳይ ከተበዳይ በማቀራረብ ልዩነታቸው በመፍታት ሰላም፣ ፍትህ የሚሰጥበት እና ዕርቅ  የሚፈፀምበት ስርዓት ሊፈጥር ችለዋል ይላሉ፡፡

እውነት ነው ሰው ልምን ይሳሳታል ባይባልም፤ ሰው ነውና ስህተቱ እንዳይደገም፣ በማስተማር ማረም አማራጭ ያልተገኘለት ዘመን ተሽጋሪ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ነው፡፡ የዕርቅ ስነ ስርዓት በየአከባቢው የየራሱ ስነ ስርዓት፣ አፈፃፀም፣ ስፋትና አገልግሎት ቢኖረዉም በአለም ህዝቦች ሲተገበር የመጣ የፍትህ ስርዓት ነው፡፡

በሀገራችንም ቢሆን በተመሳሳይ በየአከባቢው በተለያዩ ብሄረሰቦች የየራሳቸው የዕርቅ ስርዓት እንዳላቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከሚታወቁ አንድ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በጥንታዊ የ፸ እንደርታ ትልቅ ግዛት የሚገኝ በሰፊው የሚታወቅ የፍትህና የዕቅር ስርዓት የእንደርታ ዕርቅ መሆኑን ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ፁሁፍ ስለ ባህላዊ የእንደርታ ዕርቅ ስነ ስርዓት ከብዙ በአጭሩ የምናይበት ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ - አንድ

## “ዕርቂ እንደርታ”

## የእንደርታ ዕርቅ የት አከባቢ የሚገኝ የዕርቅ ስርዓት ነው?

የእንደርታ ዕርቅ በእንደርታ (፸ እንደርታ) ተብሎ በሚታወቅ አንድ በሰሜን የሀገሪቱ ክፍል የሚገኝ ጥንታዊ የትግራይ ትልቅ ክፍለ ግዛት አካባቢ ሲሆን ግዛት ስፋት ወሰኑ በየግዜው ሲሰፋና ሲጠብ የመጣ ዋና ማእከሉ ተብሎ የሚታወቅበት ግና በ**ሰሜን** ዓጋመ አውራጃ (በአሁኑ ምስራቃዊ ዞን)፤ **በምስራቅ አፋር ክልል (በአሁኑ ዞን ሁለት)፣ በደቡብ** ራያ አውራጃ (በአሁኑ ደቡባዊ ዞን) እና በአማራ ክልል (አገው ብሄር)፤ **በምዕራብ** ተምቤን አውራጃ (በአሁኑ ማእከላዊ ዞን) ማእከሉ *መቐለ* እና የ*መቐለ* ዙርያ የሚያጠቃልል በጣም ሰፊ ግዛት ነው፡፡ የእንደርታ ዕርቅ ዋና መነሻው የሚያገለግልበት በ፸ እንደርታ ይሁን እንጂ በመላ ትግራይ እና በሀገራችን ሰሜኑና ሰሜን ምስራቅ አካባቢ በስፋት የሚታወቅና የሚያገለግል ስርዓት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እንደርታ ማለት **<u>እንዳ-ርታዕ</u>**[1] ከሚል ቃል የመጣ <u>“እንዳ”</u> እና <u>“ርታዕ”</u> የሚሉ የትግርኛና የግእዝ የሁለቱ ጣምራ ቃል ነው፡፡ ትርጉም “**እንዳ**” ማለት <u>“የነ ወይም የ”</u> የሚል ጠቋሚ ቃል ሲሆን “**ርታዕ**” ማለት ደግሞ በግእዝ ቋንቋ ረትዐ፣ ርትዒ፣ ርትዕ ከሚል የወጣ ነው ትርጉም ድል አደረገ፣ ድል ተቀናጀ፣ አሸነፈ፤ ረታ ማለት ሲሆን እንዳ-ርታዕ (እንደርታ) የርትዕ፣ የፍትህ፣ የእውቀትና ብልሀት አከባቢ ማለት ሲሆን የማህበረሰብ መለያ ባህሪና ሰፊ ታሪክ፣ ባህል የሚገልፅ መጠርያ ስም ነው፡፡ እንደ ሁለተኛ መጠርያ የሚጠቀሙት የስርዓት፣ የግዛትና የማንነት መገለጫ ስም የሚጠቀሙበት **፸ (ሰባ) እንደርታ**[2] ነው፡፡

፸ (ሰባ) እንደርታ ማለት የአንድ ማህበረሰብ የስልጣኔና ጠንካራነት የማንነት መገለጫ በሆነው በዲሞክራሲያዊ መንገድ ከየአከባቢው (ገረብ) በህዝብ የሚመረጡ ፸ (ሰባ) እንደ ስራ ፈፃሚ ተወካይ የሀገር ሽማግሌዎች ያለው ያስተዳደር ስርዓት ነው፡፡ ይህ ፸ ቁጥር የራሱ ትርጉምና ታሪካዊ ይዘት ያለው እንጂ በአጋጣሚ የተሰጠ አይደለም፡፡ ቁጥሩ በግዜ ሂደት፣ በግዛት መስፋትና መጥበብ የማይቀየር ምክንያታዊ፣ ጥንታዊና ታሪካዊ የተወካዮች የብዛት መጠን ነው፡፡ እነዚህ ተወካዮች በትላልቅ ሀገራዊ ጉዳይ የሚመክሩና የሚወስኑ ተሰሚነትና ተአማኒነት ያላቸው ከገዢ መደቡ (አስተዳደር) ጋር ውሱን ስልጣን የሚጋሩ ነበሩ፡፡

የሀገር ሽማግሌዎቹ በብዙ መስፈርቶች የተመረጡ የማስተዳደር ልምድና እውቀት ያላቸው፤ ለፍትህና ለእውነት የቆሙ፣ በቅንነት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ የፈረስ ምሳ (ምሳሕ ፈረስ) ተብሎ የሚታወቅ በዓመት ሁለት ግዜ የሚሰጣቸው **እንደ ደመወዝ**[3] ነበራቸው፡፡ የተለያዩ መተዳደርያ ስርዓትና ህጎች (ስሪት) በማውጣት ያውጃሉ፤ ጠቃሚ ምክረ ሀሳቦችና የህዝብ ጥያቄዎች ያቀርባሉ፡፡ የሁሉም አካባቢ ማህበረሰብ ሁሌ የእንደርታ ታላላቆች ምን አሉ “ዓበይቲ እንደርታ ታይ በሉ” እያለ አዲስ ብልሃትና ውሳኔ ይጠብቃቸው ነበር፡፡ በድምበር ተሻጋሪ ግጭቶች ዕርቅ ይፈፅማሉ፡፡

ከአክሱም ዘመነ መንግስት የውድቀት ታሪክ በኋላ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ጠንካራ ማህበረ ኢኮኖሚና የፖለቲካ ማእከል በመሆን የቀጠለ፤ ሚዛኑ በማስጠበቅ ከላስታ በዛግዌ ስርወ መንግስት ዘመን ተመጣጣኝ ሀይል በመያዝ የተለያዩ ስርዓተ ክብር፣ ባህል፣ የተለያዩ ቅርሶች በክብር ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር በማድረግ ታሪክ የማይረሳው ጉልህ

---

[1] ቀስ የቀኝ ጌታ ይምረሃ ገብረማርያም፣ የእንደርታ ስያሜ የአመጣጥ ዝርዝር ትርጉም እንዳብራሩት “እንዳ ርታዕ”
[2] ቀስ የቀኝ ጌታ ይምረሃ ገብረ ማርያም፣ በዝርዝሩ እንዳብራሩት
[3] ሃለቃ ካሳ ፀጋይ

አስተዋፅኦ ያደረገ፤ ማንነቱና ግዛቱ በጠላት ሳያስደፍር በጀግንነትና በቆራጥነት ከባድ መስዋእት በመክፈል ሀገር ጠብቆ ያስረከበ ባለውለታና የሰፊ ታሪክ ባለቤት ህዝብ ነው፡፡

*"የመካከለኛው ዘመን የኢዮጵያ ታሪክ በምንመረምርበት ጊዜ የትግርኛ ተናጋሪዎች መጠርያ አካባቢዎች እንደርታ፣ ተምቤን እና ሰሃርቲ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ እንዲያዉም በአፄ አምደፅዮን ዘመነ መንግስት (1306-36) ከትግራይ አካባቢዎች የታወቀው እንደርታ ነበር"፡፡*[4]

የእንደርታ ህዝብ **የትግርኛ ቋንቋ** ተናጋሪ ሲሆን በሁሉም የትግራይ አካባቢ ተወዳጅ፣ ለሁሉም የትግራይ አካባቢ በቀላሉ የሚረዱት፣ በጣም ተወዳጅ፣ የአክብሮት፣ የፍቅር መገለጫ የሆነው ለስለስ ያለ ጣፋጭ አንደበት (ላዛ) ያለው ነው፡፡ "ላዛ እንደርታስ ካልተሙግተሉ" ይሉታል፡፡ ይህ ማለት አንደበተ ርቱ እና ታፋጭ አንደበት (ላዛ) ስላለው ከስሜት ነፃ ስለሚያደርግ ለሙግት፣ ለማሳመን እንዲጠቀሙበት ይመኙበታል፡፡ የእንደርታ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ በንግድ (ጨው)፣ በእርሻና በእንስሳት እርባታ የሚተዳደር ሰፊ ማሕበረሰብ ነው፡፡

በእንደርታ ሲባል በስፋት የሚታወቅበት ባህል በጣም ትሁት፣ ሰው አክባሪ፣ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለው፣ በጣም ፍትሃዊ እና አዋቂ መሆናቸው ነው፡፡ የማስታረቅ፣ የማስተዳደር፣ የባህላዊ አለባበሱና ልብሱ (ጋቢ)፣ የአሸንዳ በዓል፣ የግብር መክፈል ስርዓት፣ የማህበራዊ ትስስሩ እና መደጋገፉ (በትረ ጉሳ) ወዘተ ተወዳጅ ባህሎች አሉት፡፡

በእንደርታ የሚታወቁ ዋና ዋና መገለጫዎች (ገፅታዎች) ለማየት በሰንጠረዡ ተካትቷል

| ተቁ | በስፋት የሚታወቁባቸው ገፅታዎች (ታሪክ፣ ባህልና ቅርስ) | የሚታወቁበት መጠርያ |
|---|---|---|
| 1 | ባህላዊ ስነ-ስርዓት ዕርቅና ፍትህ | ዕርቂ እንደርታ |
| 2 | ባህላዊ ዲሞክራሲያዊ የህዝብ ተወካዮች የአስተዳደር ስርዓት | ሕጊ ፸ እንደርታ |
| 3 | የጨው ንግድ ስርዓት፤ የእንደርታ ወጣቶች ጥንካሬ መገለጫ | አርሆ እንደርታ፤ ረገድ |
| 4 | በበዓል-ጋዳ የሚወሰን የግብር አከፋፈል ስርዓት በእንደርታ | ስርዓት ግብሪ  እንደርታ |
| 5 | ጥንታዊ የመሬት አስተዳደር ስርዓት በእንደርታ | ጩጉራፍ ጎሰስ |
| 6 | በብዛት የሚታወቅ ተወዳጅና ተመራጭ የምግብ ዓይነት | ጎጎ (ሕምባሻ) እንደርታ |
| 7 | የእንደርታ የመከላከል ልዩ ብቃት መለያ የሆነው ድርብ ጋሻ | በዓል ድርብ ዋልታ |
| 8 | ጥንታዊ የብልሀትና ጥበብ መገለጫ ባህላዊ የእግር ጫማ | ሳእኒ እንደርታ |
| 9 | ምክራቸው፣ ውሳኔአቸው የሚከበር፣አንድነታቸውና ታማኝነታቸው | እንደርታ ሓደ ልቦም |
| 10 | የመደገፍ፣ መተባበር ነባር ባህላዊ የእንደርታ ገበሬ የስራ ባህል | ልፍንቲ |
| 11 | ግዜ የማይሰጥ፣ የነፃ ድጋፍ እና እገዛ የሚያስፈልገው ገበሬ ለሆነ | ኦፎራ |
| 12 | የማሕበራዊ ዋስትና ስርዓት (ለተቸገሩ፣ ኣካል ጉዳተኞች ለማገዝ) | በትሪ ጉሳ (ዝርያ) |
| 13 | ለአርሆ ተጓዥ ስንቅ፣ ለእረኛ፣የማይበላሽ ጣፋጭ የበረሀ ምግብ | ብርኩታ እንደርታ |
| 14 | ጥንታዊ የሰው መኖርያ የቤት አሰራር ዘዴ (ጥበብ) | ሂድሞ (ሀዳሙ) እንደርታ |
| 15 | ወጣት ጥንካሬው፣ ችሎታው የሚለካበት ባህላዊ የማጨት ሂደት | ኣብ ኢድ ምእታው |
| 16 | ባህላዊ የስራ ተቀጣሪ፣ የስራና አሰሪ ውል ስርዓት | ውዕል ዳባ ሰላማ |
| 17 | ጥንታዊ ያና፣ሓወልቶች፣ የቤተ መንግስቲ ቅርሶችና ገዳማት | ታሪካዊ ሓድጊ እንደርታ |
| 18 | የሊቃውንት፣ ጀግኖች፣ የነገስታት፣ የመሳፍንት ሀገር | ታሪክ ዓበይቲ እንደርታ |
| 19 | ተወዳጅ፣ ለሁሉ ቀላል፣ ያደገ ቋንቋና ላዛ ትግርኛ | ቋንቋ፣ ላዛ እንደርታ |
| 20 | የነገስት፣ የራሶች እና የበዓል ጋዳዎች ሀገር | ሰብ ብልሓት፣ሓለውቲ ዓዲ |

[4] መድኋኔ ታደሰ፣ 1992

# ምዕራፍ - ሁለት

## ዕርቂ እንደርታ ባህላዊ ስነ-ስርዓቱ ምን ይመስላል?

የእንደርታ ዕርቅ ሀገር በቀል (Indigenous) ባህላዊ ስርዓቶች ከሚባሉ ባህላዊ የዕርቅና ፍትህ ተቋም ሲሆን የኣንድ ማህበረሰብ የስልጣኔ መገለጫ፣ የዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ደረጃ የሚያሳይ ስርዓት ነው። የእንደርታ ዕቅር ማለት እንደርታ ተብሎ በሚታወቅ አከባቢ ወይ ህዝብ የአስተዳደራዊ ግዛት ውስጥ የተፈጠረ፣ የሚታወቅ እና የሚተገበር ቢሆንም በሰፊ ትግራይ አከባቢና አጎራባች ህዝቦች የሚያገለግል ሰፊ፣ ረቂቅና በሚዛናውነቱ፣ ፍትሃዊነቱ የሚታወቅ ባህላዊ የዕርቅና ፍትህ ጥንታዊ ስርዓት ነው።

የእንደርታ ዕርቅ መስማምያ፣ የግጭት መፍቻ፣ የለባሞች ምክር፣ ፍትሃዊ ውሳኔ፣ የእኩልነት ፍርድ፣ የዘላቂ ሰላም መሰረት ነው። ይህ እውነተኛ በዳይና ተበዳይ ለይቶ፣ በጥፋቱ ልክ ፍትሀዊ ማስተማርያ ውሳኔ የሚሰጥበት ስርዓት እንጂ የተፈጠረውና የደረሰው ጉዳት እኩል ቀጥቶ የሚያስታርቅ ማለት አይደለም።

የእንደርታ ዕርቅ የግጭት ማስወገጃ (መፍቻ) ብቻ ሳይሆን በጣም ሰፊና ረቂቅ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ማህበራዊ አገልግሎትም ጭምር የሚያገለግል ስርዓት ነው። በሀገራችን ይሁን በትግራይ በሰፊው ከሚታወቁ ባህላዊ ስርዓት አንድ ሲሆን ዋና ዓላማው የተጋጩ፣ ያልተስማሙ፤ ግለሰዎች፣ ቡድኖችና ጎሳ በማስታረቅ ሰላም መፍጠር፤ ልዩነቶች በማጥበብ ማስማማት፣ ማግከርና መርዳት ነው፤ የእንደርታ ዕርቅ ከተባለ ዕርቅ ከልብ ነው፣ ዕርቅ በችኮላ፣ በመደባበስ አይፈፀምም፣ ሳይጣራ፣ ሳይታወቅ ፍፁም አይፈፀምም። ይህ ዕርቅ በዳይ በደሉ አምኖ፣ ተፀፅቶ አስታርቁኝ ሲል እና ተበዳይ ከልቡ አምኖ ሲቀበል ብቻ የሚፈፀም ስርዓት ነው።

በሀገራችን በተለይ በትግራይ በሰፊው የሚታወቅ፣ የሚተገበር፣ ከግጭት አፈታት አልፎ በማህበራዊ፣ ኢኮኖምያዊና ፖለቲካዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን በፍትሃዊነቱ. ሚዛናዊነቱ፣ እኩልነቱ የሚመረጥ ጥንታዊ ሲሆን እስካሁን በጥቅም ላይ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ባህላዊ የዕርቅና የፍትህ ስርዓት ነው።

### 2.1 የእንደርታ ዕርቅ አጀማመር

የእንደርታ ዕርቅ መቼ ተጀመረ? የእንደርታ ዕርቅ ሀገር በቀል (Indigenous) ባህላዊ ስርዓት ነው። ስርዓቱ ከ13ኛው ክ/ዘመን በፊት የነበረ ቢሆንም በትክክል በየትኛው ዘበነ መንግስት፣ እንደተጀመረ በግልፅ የሚያስረዳ በታሪክ የተፃፈ ሰነድ እስካሁን አልተገኘም። ይሁን እንጂ ረጅም ዕድሜና ጥንታዊ ስርዓት ስለመሆኑ በተዘዋዋሪ የሚያስረዱ ብዙ የተለያዩ መረጃዎች በማየት ማረጋገጥ ይቻላል።

ጥንታዊ የእንደርታ ግዛት (Enderta Kingdom) ተብሎ የሚታወቅ ከመኖሩ ጋር ተያይዞ ጠንካራና በርካታ ስርዓት የነበረው በመሆኑ የዕርቅ ስርዓቱ ጥንታዊ ስለመሆኑ አያከራክርም። በዚህ መሰረት የተወሰኑትን እንደማሳያ ለመጥቀስ ያህል፡-

ሀ. ቅድመ ዘመነ ስልጣኔ አክሱም የነበረው በዝርዝር ባይገኝም ዘመነ ስልጣኔ አክሱም ከተዳከመ በኋላ ግና በግልፅ ጠንክሮ የወጣ (የቀጠለ) ጥንታዊ የእንደርታ ሰፊ ግዛት፣ የብዙ ታሪክና ስርዓተ ክብር ባለቤት መሆኑ እንደ አንድ ጠንካራ መረጃ መሆን ይችላል።

**ለ.** በዚህ የእንደርታ ማሕበረሰብ አከባቢ የተፈጠሩ ብዙ ሊቃውንት፣ ጠንካራ አስተዳዳሪዎች በመኖራቸው ምክንያት፣ በ13ኛው ክ/ዘመን በሃገራችን ኢትዮጵያ የመጀመርያው በፅሑፍ የሰፈረ ሕግ ክብረ ነገስት በግእዝ ተርጉመው የተጠቀሙ አካባቢ መሆናቸው፡፡

**ሐ.** እንደርታ በ14ኛው ክ/ዘመን አካባቢ የነበረው የማህበረ መነኮሳት ደቂቀ እስጢፋኖስ ስደትና የደረሰው መከራ ከንጉስ አፄ ዘርአያኢቆብ የነበረው አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ዕርቅ የጀመሩና በመጨረሻ ከጥቃት የተከላከሉ መሆናቸው፡፡

**መ.** መነሻቸው ከጫፍ ቀይ ባህር የነበሩ ከእንደርታ የሚዋሰኑ ኦሞለ የተባሉ የአፋር ጎሳ በድርቅና በግጦሽ ፍለጋ ምክንያት የሚፈጠረው ግጭት በዕርቅ በአቦ ገረብ ይፈቱ እንደነበር ታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡

ባጭሩ የዘመናዊ ህጎች መነሻ የሃይማኖት ተቋማት በመሆናቸው እና ይህ አካባቢ የክርስትያንና የሙስሊም እምነት ቀድመው የገቡበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ በሕገ ኦሪት፣ በሀዲስ ኪዳን፣ቁርአንና ስርዓተ መንግስታት ሲተገብር ለመጣ የሰለጠነ ማህበረሰብ የዕርቅ ስነ-ስርዓት ጥንታዊ ስለመሆኑ አያጠራጥርም፡፡

## 2.2 የእንደርታ ዕርቅ ይዘትና ሂደቱ

### 2.2.1 የእንደርታ ዕርቅ ወሰን ተሻጋሪ መሆኑ

ከስሙ ለመረዳት እንደሚቻለው ስም ብቻ ሳይሆን ጠቋሚም ነው፡፡ በብዛት የእንደርታ ዕርቅ ብለው የሚጠሩት ራሳቸው እንደርቶት (የእንደርታ ማህበረሰብ) ሳይሆን ከእንደርታ አካባቢ ውጪ ያሉ አካባቢዎች ናቸው፡፡ ዘላቂ ሰላም መፍትሄ ስለሚያመጣ፣ በግጭት አፈታት ዘዴው ታዋቂ እና ተመራጭ በመሆኑ ምክንያት ከትግራይ ብቻ ሳይሆን ከትግራይ ውጪ ተሻግረው ለዕርቀ ሰላም ታራቂዎች በቀጠሮ ይመጡ ነበር፡፡ በአጎራባች ህዝቦች አፋር፣ አገው እንዲሁም በአማራ ወሎ፣ ከሸዋ፣ ጎጃምና ጎንደር ድረስ ያስታርቁ ነበር፡፡ "ዕርቂ ለይቓሪ ብዓበይቲ እንደርታ ወሰን ተሸጋሪ"[5] ይባላል ትርጉሙ ዕርቅ ላይቀር በወሰን ተሸጋሪው በእንደርታ የሀገር ሽማግሌዎች ማለት ነው፡፡

### 2.2.2 "ኣቦ ገረብ"[6] (ቋሚ የወሰን የሀገር ሽማግሌዎች)

በእንደርታ ዕርቅ ውስጥ አንድ ትልቅ የሀገር ሽማግሌዎች ስርዓት አቦ ገረብ ይባላል፡፡ አቦ ገረብ በህዝብ የሚመረጡ ቋሚ ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ውጭና በውስጥ የወሰን ግጭቶች፣ አለመስማማቶች የሚፈታ የዕርቅና የፍትህ ተቋም ነው፡፡ ከአፋር፣ አገውና አማራ ብሄር የሚያጋጥም የወሰን ግጭት ከጥንት ጀምሮ እስካሁን በአቦ ገረብ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ዳኛና ፍርድ ቤት የለዉም፡፡ በወሰን የተፈጠሩ የጥንት ታሪኮች ሲታዩ "በኦሞለ፣ ዶብዓና የኦሮሞ ብሄር ግጭቶች"[7] የተፈቱበት አባቶች ይተርካሉ፡፡ የአቦ ገረብ አጀማመርና በስፋት የሚታወቅበት በእንደርታ ቢሆንም በአሁኑ ግዜ በሶስት ዞኖች (ደቡብ ምስራቅ፣ ምስራቅና በደቡብ) እስካሁን ይተገበራል፡፡

---

[5] ሃለቃ ካሳ ፀጋይ

[6] **አቦ ገረብ** ማለት በህዝብ የሚመረጡ ቋሚ የሀገር ሽማግሌዎች ሲሆኑ በስነ ምግባራቸው፣ የአከባቢው ታሪክ ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ቂም በቀል የሌላቸው፣ ወደ ተጠሩበት በጓዝ የሚችሉ፣ ተአማኒና ተወዳጅ የሆኑ በውስጥና በውጭ የወሰን ግጭቶች፣ ከብሄር በአዋሳኝ ጉዳዮች የሚያስታርቁ፣ የሚዳኙ በሁለቱ ወገን የሚመረጡ ናቸው፡፡ በሁለቱ ወገን የሚመረጡ ማለት ለምሳሌ የአፋርና የእንደርታ ሲሆኑ የእንደርታ አቦ ገረብ በእንደርታ እና በአፋር፣ የአፋር ደግሞ በአፋርና በእንደርታ የሚመረጡ ማለት ነው፡፡

[7] **ደስታ በርሀ**፣ አቦ ገረብ

### 2.2.3 በሽምግልና የሚሳተፉ ፆታ፣ ዕድሜ፣ እምነትና ስልጣን

በዕርቅ ስነ ስርዓቱ ሁሉም የማህበረሰቡ መደብ እንደ አቅሙና በየደረጃው እንደ አስታራቂ ሆኖ ቀርቦ የሚሳተፍበት መብት አለው። እናቶች (ሴቶች) ከአቦ ገረብ፣ ከነብስ ግድያና የሩቅ ጉዞ የሚጠይቅ ዕርቅ ውጪ በሌላው ይሳተፋሉ፣ ያስታርቃሉ። ከቀላልና ከባድ የዕርቅ ሁኔታ ከህፃናትና የሀገር ሽማግሌዎች የመሳተፍ ሙሉ መብት አላቸው። በዕርቅ ግዜ የአስታራቂ እምነት ገደብ የለዉም። የተፈለገ፣ የተመረጠ ከሆነ እና በጣም አስተዋይ፣ ፍቃደኛ፣ ብቃትና ችሎታ ካለው ከወገንተኝነት ነፃ ከሆነ ማስታረቅ ይችላል። ነገስታት፣መኳንንትና መሳፍንት በዕርቅ ግዜ በታዛቢነት ወይ በአስታራቂነት ሆነው ይሳተፋሉ ያስታርቃሉ።

### 2.2.4 የእንደርታ ዕርቅ ለችድመ ግጭት መፍትሄ የሚሰጥ መሆኑ

ገና ወደ ጉዳት ደረጃ ያልደረሰ፣ ፉክክር፣ የመጠባበቅ፣ የመፈላለግ፣ ወይ የቆየ ቂም በቀል የሚቀሰቅስ ሁኔታ መነሳቱ ሲሰማ፣ ጥቆማ ሲደርስ የሀገር ሽማግሌዎች ግጭቱ ከተነሳ አደገኛነቱ አስቀድመው በመረዳት ዕቅር እንዲደረግ ይጠራሉ ይመጣሉ።

በእንደርታ ዕርቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው አንዱ ይህ አይነት ዕርቅ ነው። በተለይ የጎሳ፣ የወሰን፣ የመሬት፣ በሴት ልጅ፣ ጎረቤት፣ የቡድን እና ወጣት ዕድሜ ከሆነ በጣም አደገኛ በመሆኑ ተሎ ዕርቅ እንዲፈፀም ያደርጋሉ።

### 2.2.5 የእንደርታ ዕርቅ እስካሁን አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ

የእንደርታ ዕርቅ በማህበረሰቡ ይሁን በመንግስት ያለው ጥቅም ስለሚታመንበት አሁን በቅርቡ በጣም ይሰራበታል። ለዚህ እንደ ዋና ማሳያ በፍርድ ቤት የተፃፈ "**መጀመርታ ዕርቂ እንደርታ**" ማለት ፍርድ ቤት ከመምጣታችሁ በፊት በእንደርታ ዕርቅ ፍቱት ማለት ነው። በተወሰነ መልኩ የዘመናዊ ሕግ ከመግባቱ ጋር ተያይዞ ብዙ የወንጀል ነክ ግጭቶች የማየት መብቱ የተገደበ በመሆኑ የቀነሰ ቢሆንም በአቦ ገረብ ሙሉ በሙሉ፣ በማስማማት፣ በውሎችና ቀለል ያሉ ጉዳዮች በባህላዊ የዕርቅ ስርዓቱ እስካሁን እየታየ፣ እያገለገለ ይገኛል።

በተለይ በወሰን እና በብሄር ለሚፈጠር ጉዳይ የሚያዩ የሀገር ሽማግሌዎች (ኣቦ ገረባት) በስርዓት እስካሁን ሙሉ በሙሉ በስራ ተግባር ላይ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ስርአት ነው።

### 2.2.6 የእንደርታ ዕርቅ የዘላቂ ሰላም ተመራጭ ሥርዓት መሆኑ

በእንደርታ ዕርቅ የበዳይና ተበዳይ ሁኔታ በጥልቀት የሚመረምርበት ስርዓት አለበት። የግጭቱ ወይ አለመስማማቱ ዋና መነሻ ጉዳይ፣ እንዴትና በምን ምክንያት እንደተፈጠረ ይመረምራል። በተለይ ግጭቱ የተነሳው በተንኮል፣ በቂም በቀል እና ሆን ተብሎ ከሆነ በጥልቀት ይታያል። እዚህ ላይ በችኮላ፣ በመደፋፈን፣ ብውግንና ይሁን ዝምድና ታይቶ ችላ የሚባልበት ቀዳዳ በፍፁም የለም። ይህ ሁሉ ከተደረገ በኋላ በዳዩ አምኖ ተቀብሎ ካልቀረበ እርቅ አይታሰብም።

ፍርጥርጡ ከወጣ በኋላ በሁለቱ ወገን ከልብ ከተቀበሉት በኋላ የእርቁ ስነ ስርዓት እንዲፈፀም ይደረጋል። በዚህ ዕርቅ የሚቀር ነገር የለም፣ ዘመድ አዝማድ ቅሬታ አለኝ የሚልና ቅሬታ ይኖረዋል የተባለ ሁሉ እንዲታረቅ ይደረጋል። በዚህ ምክንያት ምንም አይነት የመጠራጠርና የስጋት ሁኔታ ስለማይፈጠር በሁሉም ወገን ተማምኖ በሰላም ይኖራል። "ድሕሪ ዕርቂ እንደርታ የለይ ቅሬታ" ይሉታል ከእንደርታ ዕርቅ በኋላ ቅሬታ የለም ለማለት ነው።

### 2.2.7 የእንደርታ ዕርቅእንደ የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ ያገለግል ነበር (እንደ ሰበር)

የእንደርታ የሀገር ሽማግሌዎች ለእንደርታ አከባቢ ብቻ የሚያገለግሉ ሳይሆኑ በየአቅጣጫው ተሞክረው መፍታት ያልቻሉ ከባድና ውስብስብ ጉዳዮች ያያሉ ይፈታሉ። መስማማት፣ መታረቅ ያልቻሉ ጉዳዮች ለመጨረሻ ግዜ በእንደርታ እንዲታይ ብለው ተጉዘው ይመጡ ነበር።

ብዙ ግዜ የታየና የተሞከረ ይህ ከባድ በመሆኑ ከእንደርታ ውጪ በሌላ አይፈታም ተብሎ ይታመናል፡፡

ታራቂዎች ወስነው ሲመጡ የመጨረሻ መሆኑን አምነው ነው የሚመጡ፡፡ የእንደርታ የሀገር ሽማግሌዎች ካዩት ፍትሃዊ ውሳኔ እና ዘላቂ ሰላም ያገኛሉ፡፡ "ድሕሪ ዕርቂ እንደርታ ላብ ላዕለዋይ ጎይታ" ነው የሚባለው፣ ይህ ማለት ከእንደርታ ዕርቅ በኋላ ደወ ላይኛው ጌታ ማለት በምድር የመጨረሻው የዕርቅ ፍትሃዊ ውሳኔ እንደ ሰበር ለማለት ነበር፡፡

### 2.2.8 የእንደርታ ዕርቅ ሰፊ ተጠቃሚነት፣ ተቀባይነትና ታዋቂነት አለው

በትግራይ ሙሉ ከትልቅ እስከ ትንሽ የፍትህ፣ ስምምነት፣ ማስታረቅና ዘላቂ ሰላም ሲፈልጉ ሁሌ በፊት የሚመጣላቸው፣ የሚታወቅ፣ የሚተማመኑበት የእንደርታ ዕርቀ ነው፡፡ ልዩነታቸው ለማጥበብ "ዕርቂ እንደርታ ንግበራ" ነው የሚሉት፣ የእንደርታ ዕርቅ እናድርጋት ይላሉ፡፡

በፍትሃዊነቱ ምክንያት በትግራይ ስለሚታወቅ በተግባር ይጠቀሙበታል፡፡ በእንደርታ ዕርቅ የሚወሰን ውሳኔ ተቀባይነት ተአማኒነት አለው፡፡ በተለይ ቀለል ያሉ ግጭቶች፣ ለማስማማት፣ በገበያ፣ ለማቀራረብና ለማዋዋል ይጠቀሙበታል፡፡

### 2.2.9 የእንደርታ ዕርቅ ለሁሉም በእኩልነት ሳይሸፋፍን የሚዳኝበት መሆኑ

የእንደርታ ዕርቅ የራስ ስሪት ያለው ስርዓት በመሆኑ ስሪቱ አስገዳጅና በትክክል የሚተገበሩ ናቸው፡፡ ከስሪቶቹ ዋና ዋና ከሚባሉ ሰው ሁሉ በእኩል ይዳኛል፤ ሀፍታም፣ ድሃ፣ መስፍን፣ ንጉስ ወዘተ የሚባል ነገር የለም፡፡ የፈለገ ዓይነት ሰብ፣ ቡድን ና ጎሳ ቢሆን ጥፋተኛ በጥፋቱ ታውቆ፣ ጥፋቱ አምኖ፣ በልክና ትክክለኛ ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር ተደባብሶ፣ ተሸፋፍኖ የሚያልፍ ዕርቅ የለም፡፡

"ኣብ ዕርቀ ሰነያ ኹሉ ዕርያ" እና "ኣብ ዕርቂ ፬ እንደርታ የለይ ጎይታ" ይሉታል፡፡ ይህ ማለት በዕርቅ እና መስማማት ሁሉም እኩል ነው፤ በ፬ እንደርታ ዕርቅ ጌታ የለም እንደ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ለሰው ሲሉ ሰውን መበደል በጣም ይፀየፋሉ ስለ እውነት ይፈርዳሉ፡፡ "ሓቂ ፅዋ ምሳሕ አቦይዝጊ" ይሉታል፤ እውነቱን መናገር የእግዚአብሄር ምሳ ነው ለማለት ነው፡፡

### 2.2.10 የእንደርታ ዕርቅ ለሁለት በመባል ይታወቃል

የእንደርታ ዕርቅ ሁለተኛ ስሙ "ዕርቂ እንደርታ ልኽልተ" የእንደርታ ዕርቅ ለሁለት እንደ ማለት ነው፡፡ የእንደርታ ዕርቅ በሁለቱም በዳይና ተበዳይ ወይ ሁለት የማይስማሙ ወደ አንድ በማምጣት ካለ ምንም ቅሬታ ሳይፈጥር እኩል ያስታርቃል፣ ያስማማል እንጂ እኹል አይዳኝም፡፡ የእንደርታ ዕርቅ እንደ ፍርድ ቤት ለአንድ ወገን፣ ውሳኔ የሚሰጥ አይደለም፡፡

### 2.2.11 የእንደርታ ዕርቅ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች ያስወግዳል

የእንደርታ ሽማግሌዎች ሰውን ከሰው የሚለያይ፣ ማህበራዊ ግኑኝነት የሚያሻክር፣ የአካባቢ ፀጥታን የሚያውክ ነገር በማስተዋል እና በመወያየት ለማስቀረት ዘላቂ መፍትሄ እንዲሰጥ ይመክራሉ ይወስናሉ፡፡

በእንደርታ ዕርቅ ሁሌም የሚጠቀስ በጣም ውጤታማ ስራ የተሰራው በ1934 ዓ.ም በገረብ ደልገና የተባለ ቦታ የመጀመርያው የወያኔ ስምምነት (የገበሬው አመፅ) የረጅም ግዜ ታሪክ የነበረው በአፋርና በትግራይ ብሄር የነበረው ባህላዊ ጎጂ ድርጊት ***ጋዝ***[8] የሚባል የእንስሳ ዝርፍያና የሰው ግድያ ጉዳት ብቻ እንጂ አንድ ጥቅም የለውምና ቢቀር፣ ሰላም ቢፈጠር

[8] ጋዝ የሚባል በአፋርና በትግራይ አጎራባች አውራጃዎች መካከል ከጥንት ጀምሮ የነበረ ጎጂ ባህላዊ የእንስሳት ዝርፍያ ሲሆን በሁለቱ ወገን አሸናፊና ተሸናፊ ያልነበረው በየተራ በዘመቻ መልክ የሚካሄድ ዘረፋ ነበር፡፡

በማለት ብላታ ሃይለማርያ ረዳ በሚመሩት የአቦ ገረብና የአቦ ጋዝ የሀገር ሽማግሌዎች ተስማምተው እንዲቀር የተደረገበት ወርቃማ የዕርቅ ታሪክ ነው።

### 2.2.12 የእንደርታ ዕርቅ ለሁሉም የማህበረሰብ መደብ ያገለግላል

በእንደርታ ዕርቅ የተለየ ስርዓት የለም ለሁሉም አንድ ነው። በእንደርታ ዕርቅ ፍላጎት ያለው ማንኛዉም አካል በመጨረሻው ስነ ስርዓቱ መሳተፍ ይችላል። በዓል ጋዳ፣ መኳንንት፣ መሳፍንትና ነገስታትም ጭምር በስርዓት ይሳተፋሉ ይዳኙበታል። በዕርቅ ግዜ የተለየ በስልጣን፣ ክብር በተለየ ሁኔታ የሚታይበት ምንም ምክንያት የለም። ሁሉም የህብረተሰቡ መደብ በእኩል የሚዳኝበት ሚዛናዊ የፍትህ ስርዓት ነው።

### 2.2.13 የእምነት (ሃይማኖት) ልዩነት እና እኩልነት ያከብራል፣ ያስማማል

በየተለያዩ እምነት ምክንያት ለሚፈጠሩ ልዩነቶች የማስማማት፣ የማስታረቅ ስራ ይሰራል። በታሪክ በእንደርታ የሀገር ሽማግሌዎች በዕርቅ አማካኝነት የተፈቱ ብዙ የሃይማኖት ግጭቶች አሉ።

### 2.2.14 የእንደርታ ዕርቅ ከዘመናዊ ሕግ ያለው ትስስር (ዝምድና)

በአብዛኛው ዘመናዊ ሕጎች መነሻ የሆነው ባህላዊ ስርዓቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት መሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ። የእንደርታ ዕርቅም ዝርዝሩ ስናየው በተመሳሳይ ከዘመናዊ ሕግ ጋር በቀጥታ ይገናኛል። ትልቁ ልዩነታቸው የእንደርታ ዕርቅ በሕገ ልቦና፣ በስራት (በፅሁፍ ያልሰፈረ)፣ ዘመናዊ ሕግ ደግሞ በፅሁፍ የሰፈረ በመሆኑ ብቻ ነው።

### 2.2.15 የዕርቅ ጥቅሞች

ዕርቅ ለሁለት ፍርድ ለአንድ እንደሚባለው ግጭቶት በዕርቅ ሲፈቱና ሲፈፀሙ ለሀገር (ለመንግስት)፣ ለግለ ሰው፣ ለቡድን፣ ለማሕበረሰብና ለአካባቢ ሰላም በጣም በርካታ ተጨባጭ ጥቅሞችን አለው።

**በኢኮኖምያዊ (ስነ-ቑጠባዊ)** በግጭት ምክንያት የሚወጣ ገንዘብ ወጪ በማስቀረት የኑሮ ደረጃ ያሳድጋል። ለጠበቃ፣ ለፀሓፊ፣ ለአማካሪ፣ ለመጓጓዣ፣ ለምግብ፣ ለማደርያ አልጋ ፣ ለምስክሮች አበልና ሌሎች ወጪዎች ያስቀራል።

**ጊዜህን በአግባቡ ትጠቀማለህ** ዜጎች ኑሮአቸው ለማሸነፍና ለመለወጥ ወርቃማ ግዚያቸው በስራና በልማት ማሳለፍ አለባቸው። በግጭት ምክንያት ግዚያቸው በፍርድ ቤት፣ በቀጠሮ ምልልስ፣ በእስር ቤት፣ በእግድና በስደት ማሳለፍ የለባቸዉም።

***የስነ-ኣእሙራዊ ዕረፍት ይሰጣል ከፉክክር፣*** *ከመጠባበቅና ክርክር ነፃ የሆነ አእሙሮ መልካሙን ብቻ ያስባል። ግጭትና አለመስማማት ሲያጋጥም በዕርቅ ሲጨረስ ከስሜታውነት፣ ከብስጭትና ጭንቀት፣ ሀሳብና ፀፀት፣ ከአእሙሮ ጭንቀት ትድናለህ።*

***የግልና የአካባቢ ሰላም ይጠበቃል*** *ከሰዎች ጋር ነገርና ግጭት ከሌለ የተረጋጋ ሰላማዊ ሂወት ይኖርሀል፤ የቤተሰብ፣ የአካባቢ ሰላም ይጠበቃል። የውጭ ይሁን የውስጥ ሰላምና ደህንነት ይጠበቃል። በፉክክርና እልህ አሳልፎ ሚሰጥ ግለ ሰው ይሆን ቡድን ወይ ጎሳ ሊኖር አይችልም።*

***ማሕበረሰባዊ መተሳሰርን ያጠናክራል*** *ግጭቶች በሰላማዊ ዕርቅ ከተፈቱ ከጎረቤት፣ ከጎሳ፣ የቡድንና ከአጎራባች ብሄር ያለው መተሳሰብ፣ መቀራረብና መተማመን በማጎልበት የተሳሰረ ጠንካራ ሰላምና ማሕበራዊ ግኑኝነት ይፈጠራል። እርሰ በርስ፣ አንዱ አንዱን ከማጥቃት ይልቅ እርሰ በርስ ከትቃት ይከላከላል።*

***የህዝቦች አንድነትና ድህንነት ምንጭ ይሆናል*** *ዕርቀ ሰላም ካለ ፍቅር ይነግሳል፤ ፍቅርና መተሳሰብ ካለ አንድነት ይጠናከራል፣ ጠንካራ አንድነት ካለን ደግሞ የተጠበቀ ደህንነት እንዲኖረን ያደርጋል።*

***የዘላቂ ሰላም ምንጭ ይሆናል*** *ሁሉም አለመስማማቶች፣ ቅሬታዎችና ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ በእኩልነት፣ በፍትሃዊነት በዕርቅ ከተፈቱ ቅሬታ ስለማይኖር፣ መጠራጠር፣ ዛቻና ፍራቻ ይቀርና ሰላም ብቻ ይሰፍናል።*

***ዕርቁ በአጠገባቸው፣ በሚያውቋቸው ሰዎች፣ በነፃ፣ በሚመች ቦታና ቀን ይፈፀማል*** *ብዙ ጉዞ የሌለው፣ ስራ በማይጎዳ፣ ለሁሉም በሚመች ቀንና ሰዓት ካለ ምንም ክፍያ በነፃነት ይፈፀማል። በሆነ አጋጣሚ ቀንና ቦታ ቢቀየር እንኳን ምንም ዓይነት ኪሳራ የለዉም።*

### 2.2.16 የእንደርታ ዕርቅ ከግጭት ኣፈታት ውጪ ሰፊ አገልግሎት አለው

**የእንደርታ ዕርቅ** በማህበራዊ፣ በኢኮኖምያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ በእንደርታ ግዛት ውስጥ፣ በመላ ትግራይ፣ በአጎራባች ህዝቦችና በሃይማኖት ልዩነቶች ልዩነት በማጥበብ፣ በማስማማት ይሰራል።

## ምዕራፍ - ሶስት

# የእንደርታ ዕርቅ አሁን ያለበት ሁኔታ

ዕርቂ እንደርታ (የእንደርታ ዕርቅ) ውጤታማነቱ፣ ማህበራዊ ግኑኝነት፣ ለአንድነትና ሌሎች ጥቅሞች በማህበረሰቡና በመንግስት ስለሚታመንበት እስካሁን አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

ነገር ግን የስነ ስርዓቱ ሂደት፣ ሙሉ በሙሉ እንደ ጥንቱ ባህላዊ ይዘት በጠበቀ፣ ሚዛናውነቱ፣ በተወሰነ መልኩ እየቀነሰ መሆኑ ይገልፃሉ። አሁን ከአቦ ገረብ፣ ከቀላል የወንጀል ድርጊቶች፣ ከግጭት ውጪ የሚደረጉ የማስማማትና ማማከር ውጪ የተወሳሰቡና ከባድ ወንጀሎች ከዘመናዊ የሕግ ጋር ተያይዞ በባህላዊ የዕርቅ ስርዓት የማስታረቅ ስርዓት ቀንሰዋል።

አሁን ደግሞ እንደገና የዕርቅ ጥቅሞች በማየት በውሱን መልኩ መልካም ጅማሮዎች መታየት ጀምረዋል። በፍርድ ቤቶች የእንደርታ ፍትሓዊነት፣ ሚዛናውነት ስለሚያውቁና ስለሚያምኑ ቢሮአቸው ግጭቶች ወደ ፍርድቤቶች ከመምጣታቸው በፊት በዕንደርታ ዕርቅ እንዲያዩት እንዲህ በማለት ይመክራሉ “መጀመርታ ዕርቂ እንደርታ” የሚል ፅሁፍ ይጠቀማሉ።

**አዲሱ ትውልድ** ከዚህ በተጨማሪ በዓለማቀፍ ያለው ዓለማቀፋዊነት (Globalization) የምዕራባውያን ተፅእኖ ቀላል የሚባል አይደለም። አንድ ማህበረ ኢኮኖምያዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር በሚደረገው የባህላዊ ማሕበረሰባዊ መተሳሰር በማላላት የአስተሳሰብ ለውጥ በመፍጠር በተለይ በወጣቶች ላይ የፈጠረው ተፅእኖ ዘመናዊነትና የምዕራባውያን አስተሳሰብ በመያዝ የሀገር በቀል ስርዓቶች ትኩረት ሳይሰጠው መቆየቱ። የትምህርት ስርዓቶች የባህላዊ ዕርቅና ፍትህ ያላካተቱ በመሆናቸው ይዘቱ እየቀነሰ መጥተዋል።

መንግስታዊ ተቋማት ማለት በፍትህ፣ በፀጥታ፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የህግ ኮሌጆች፣ ባህልና ቱሪዝም የተለያዩ ሚድያዎች በሃገር በቀል ባህላዊ ስርአቶች በትኩረት አለመስራትና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል አለማድረግ።

በመንግስታዊ አካላት በተለይ በፀጥታ አካላት በእርቅ ስነ ስርዓቱ ላይ፣ በአቦ ገረብ ጣልቃ በመግባት ለፖለቲካዊ ጥቅም እንዲውል ማድረግ እና የፍትህ ሚዛኑ የተዛባ እንዲሆን ጫና መፍጠር፡፡

**ባህላዊ የዕርቅ** ስርዓቶች ከማንኛዉም አካል ተፅእኖና ጣልቃ ገብነት ነፃ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡ ባለ ስልጣናት፣ ባለ ጉልበት(ሀብት)፣ የባህላዊ ዕርቁ ስሪትና መመርያ በመጣስ ለራሳቸው በሚመች፣ ስልጣናቸው ሊያራዝምላቸው የሚችል ውሳኔና ሀሳብ በማራመድ በግዝያዊነት እንዲፈታ ያደርጋሉ፡፡ ለግዝያዊ ተብሎ የሚወሰን ነገር ነገ ስለሚመለስ የዘላዊ ሰላም መሳርያ ሊሆን አይችልም፡፡

**በባህላዊ የዕርቅ ስነ ስርዓት የሚታዩ ችግሮች** በዘላቂነት ለመምፍታት ከተፈለገ የራሱ ነፃ የሆነ ግልፅ ስልጣንና ተግባር የሚኖረው ትልቅ ሀገራዊ የዕርቅ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ የፀጥታና የተለያዩ የመንግስት አካላት ጣልቃ የሚገቡበት፤ ወጣቶች ባህላዊ ስርዓቶች ለዘመናዊ ስርዓት ሁሉ መነሻ ስለመሆናቸው ጥልቅ እውቀት አለመኖራቸው፤ እውነተኛ ፍትህ የሚሰጡ ተቋማት ፤ ማንነታችን ፣ መነሻችን ስለመሆናቸው በዝርዝር የሚያስረዳ በስርዓተ ትምህርት ተካትቶ እንዲሰጥ እና እንዲያድግ የሚደረግበት መንገድ ቢተገበር የዘላቂ ሰላም ዋስትናችን ሊሆን ይችላል፡፡

የሰላም ሚኒስቴር፣ የዕርቅ ኮሚሽን፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የሕግና ፍትህ ተቋማት፣ ባህልና ቱሪዝም በአንድ ላይ ቁጭ በማለት የዕርቅ  ስርዓት ለዘላቂ ሰላም ለመዘርጋት በቅርበት በቁርጠኝነት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ - አራት

## ስለ ዕርቅ እንደ ሀገር ምን ይደረግ

**የተነሳው የዕርቅ ሃሳብ** አሁን ካለው የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ሲታይ በትክክለኛ ግዜ የተነሳ ሀሳብ ነው፡፡ የሀገሪቱ የፖለቲካ ትኩሳት፣ የተለያዩ ልዩነቶችና ፉክክሮች ሄደው ሄደው መጨረሻቸው ወደ ማንወጣበት ግጭት ሳይገባ በግዜና ጉዳት ሳያደርስ ለማብረድ ትክክለኛው መፍትሄ በዘመናዊ ሕግ ብቻ መሄድ ሳይሆን በመስማማትና በዕርቅ ብቻ ነው፡፡ ስለዚ ለዚህ ሁሉ ዋና ቁልፍ መፍትሄው ደግሞ የእንደርታ ዕርቅ ነው፡፡

ስርዓትና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ቅድሚያ የተረጋጋ ፖለቲካ፣ ሰላም ሊሰፍን ይገባል፤ ሰላም እንዲኖር ከልብ የመነጨ የሰላም ፍላጎትና ዝግጁነት ያስፈልጋል፤ ሰላም ለማምጣት ልዩነቶች ማጥበብ ዕርቀ ሰላም መፈፀም የግድ ይላል፡፡ ስለዚ የዕርቅ ሀሳቡ በትክክለኛ ግዜ የተነሳ ቀና ሀሳብና ዕቅድ ነው፡፡

**ከባህላዊ የዕርቅ ሥርዓቶቻችን** መውሰድ ያለብን እኛ ኢትዮጵያውያን የቀደምት የሰው መገኛ ብቻ ሳንሆን የቀደምት ስርዓት ባለቤቶች መሆናችን እና አዲስ የምናመጣው ስርዓት እንደሌለ ማወቅ ነው፡፡ ለሀቅ (እውነት)፣ ለፍትህ፣ ለሰላም መቆም ማለት ለሀገር ደህንነትና አንድነት፤ ለዘላቂ ሰላም ቁልፍ ነገር ስለመሆኑ እንማርበታለን፡፡ ባህላዊ ስርዓቶቻችን የዘመናዊ ሰርዓቶች መነሻ ብቻ ሳይሆኑ አሁንም በአግባቡ ብንተገብራቸው እንከን የለሽ ትክክለኛ የሰላም መንገድ መሪ ናቸው፡፡

**ይህ ፕሮጀክት** የኢትዮጵያ የትንሳኤ ለማብሰር የመጀመርያው ማንቅያ ደወል ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህ ፕሮጀክት የሀገሪቱ ለፍትህ፣ ለሰላም፣ ለዕርቅና ለስምምነት ያላትን ዝግጁነት በግልፅ የሚያሳይ ትልቅ ራዕይ ያለው ዕቅድ ነው፡፡ ባህላዊ ስርዓቶች መነሳት፣ መሰነድ፣ መዘጋጀት ማለት መነሻችን፣ ቅርሶቻችን፣ የማንነታችን መገለጫ የሆኑትን ተመልሰን ቆም ብለን የምናስብበት፣ የወደፊት ዕቅዳችን ከመነሻችን መሆን እንዳለበት ያሳያል፡፡

## ምዕራፍ - አምስት

## መደምደምያ

የእንደርታ ዕርቅ እስካሁን የሚያገለግል መሆኑ፣ ሰፊ ተጠቃሚነት፣ ታዋቂነት ያለው ስርዓት በመሆኑ ፣ ወሰን ተሻጋሪ ለብዙ ብሄር የማስማማት፣ የማስታረቅ ዓቅምና ብልሃት ያለው ባህላዊ ስርዓት ነው። የእንደርታ ዕርቅ ከየግል ጥላቻና ግጭት ውጪ በትላልቅ ሀገራዊ ውሳኔዎች ስምምነቶች ወይ አለመስማማቶች በብልሃት የመፍታት ብልሃትና ዓቅም ያለው ትልቅ ጥንታዊ ተቋም ነው።

የእንደርታ ዕርቅ ወሳኝ የዘላቂ ሰላም፣ ተአማኒና ሚዛናዊ ስርዓት መሆኑን፣ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶች የማስወገድ ችሎታ አለው።

የእንደርታ ዕርቅ አስገዳጅ በመሆኑ፣ በችኮላና በመደባበስ ሳያጣራ ውሳኔ የማይሰጥ ስርዓት ነው።
የእንደርታ ዕርቅ ለህዝቦች ድህንነት እና ለአንድነት፣ ለአካባቢ ሰላም፣ የተረጋጋ ኑሮ ለመኖር ወሳኝ ስርዓት ነው።

የእንደርታ ዕርቅ በጣም ሰፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከግጭት ውጪ በብዙ ማሕበራዊ ጉዳዮች እየገባ አገልግሎት የሚሰጥ ባህላዊ ስርዓት ነው። የእንደርታ ዕርቅ ይመክሩበታል፣ ያስማሙበታል፣ ይዋዋልበታል፣ የሰብአዊ መብት ጠበቃ ሆኖም ይሰራል። በአጭሩ የእንደርታ ዕርቅ የዘላቂ ሰላም አማራጭ የሌለው እውነተኛ መፍትሄ ስለሆነ ሊሰራበት ይገባል።

## ዋቢ


ላጲሶ ጌ. ድሌቦ/ዶክተር/። 1983 ዓ.ም።የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓት ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም 1900-1966።

ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ። 2011 ዓ.ም። ዕርቂ። ዓመታዊ መፅሄት። ዳዮ ቤት ሕትመት።

መራኸብቲ ሓፋሻት (ቲቪ ትግራይ፣ ሬድዮ ድምፂ ወያነ፣ ሬድዮ ፋና (ኤፍ ኤም)፤ መቐለ 104.4

መድሃኒኔ ታደሰ። 1991 ዓ.ም። የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት የግጭት መነሻና መድረሻ።

ማሕበር ልምዓት ቐ እንደርታ። 2011 ዓ.ም። ቦኽሪ 12 ገረባት ገረብ ደልገና።

ማሕበር መስቀል ጩምዓ። 2007 ዓ.ም። ኣከባብራ በዓል መስቀል ኣብ ጩምዓ።

ራስ ልኡል መንገሻ ስዩም። 2010 ዓ.ምየትውልድ ኣደራ። ኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ።

ሰለሞን ገ/ አረጋይ መንገሻ ስዩምና ልማት። 2007 ዓ.ም። ቤት ሕትመት ፕላኖግራፊ።

ቢሮ ፀጥታን ምምሕዳርን ብሄራዊ ክልላዊ ትግራይ። 2009 ዓ.ም። ሰላም ስራሕቲ ሕትመት ዳዮ። መፅሄት ቑፅሪ 7/

ባህላዊ ስነ ስርዓት ዕርቂ እንደርታ። 2012 ዓ.ም። ባህልን ቱሪዝምን ክልል ትግራይ፣ ብማሕበር ልምዓት ቐ እንደርታ፣ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ።

ቤት ፅሕፈት ርክብ ህዝብን መንግስትን ወረዳ እንደርታ። 2011 ዓ.ም። ብርኩታ። ቤት ሕትመት ዳዮ። መፅሄት ሕትመት ቑፅሪ 18/

ብርሃኑ ኣባዲ። 1993 ዓ.ም። ተራሮች ያንቀጠቀጠ ትውልድ ቅፅ አምስት። ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ተክለፃዲቅ መኩርያ። ፲፱፻፹፪ ዓ.ም። ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት። ኩራዝ ኣሳታሚ ድርጅት።

ካሕሳይ ገ/እግዚኣብሄር፡፡ 2008 ዓ.ም፡፡ ባህልና ክርስትያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ፡፡ በኦ/ኦ/ቤ/በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ ማደራጃ መምሪያ ማኀበረ ቅዱሳን፡፡

ካሳ ሃይለማርያም ረዳ፡፡ 2010 ዓ.ም፡፡ገረብ ዓረና ወያነ ትግራይ፡፡ ቤት ሕትመት ዩኒቨርሲቲ ኣዲስ ኣበባ፡፡

ገብረ ሥላሴ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ መዝገብ ቅዱሳን፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን፡፡

ግርማ ኤልያስ፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ ደቂቀ አስቲፋኖስና የደብረ ብርሃን ሽንጎ፡፡

(ኤፍ ኤም)፣ ሬድዮ ፋና ኣምሓርኛ (1994፣ 2011፣ 2012)

እዝኒ መሓዛ ቻዳሙን

ዓበይቲ ዓዲ/ሽማግለታት

አቦ ገረባት

መንግስታዊ መሓውር ሕጊ (ቤት ፍርዲ)

ስሪት አቦ ገረባት

ናይ ዕርቂ ብሂላት ካብ ማሕበረሰብ

ታሪካዊ ናይ ዕርቂ ቦታታት (ሓወልቲታት)

**ሥእል 1፣** በእንደርታ የቀላል ግጭት ዕርቅ ስነ ስርዓት ሲፈፀም የሚያሳይ ፎቶ ነው።



**ሥእል 2፣** በእንደርታ ግዛት የተፈፀመ የነብስ ግድያ ዕርቅ ስነ ስርዓት የሚያሳይ ፎቶ ነው።



**ሥእል 3፣**

**ይህ ሃወልት ትግራይ ከአፋር ጋር በየመጀመርያ የወያነ ውል ጎጂ ባህላዊ ድርጊት የጋዝ ወራር** በዕንደርታ ዕርቅ የቀረበት በ1934 ዓ.ም የተፈፀመ ታሪካዊ ሲሆን በ1982 ዓ.ም የተሰራ ነው፡፡

